ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ታህሣሥ 11 ቀን 2001 ዓ.ም.

- የወያኔዉ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር ታምራት ላይኔ ከ12 ዓመታት እስራት በኋላ ተፈታ፣ እነመለሰ በዉስጣቸዉ የተከሰተዉን የፖለቲካ ሽኩቻ እንዳያጠዘዉ ከፍተኛ ስጋ ስለገባቸዉ እያስፈራሩት መሆኑ ተጋለጠ፣

- ኤፈርት የተባለዉ የህወሀት ግዙፍ ድርጅት ዓመታዊ ትርፉን ለህወሀት ጥቂት ከፍተኛ ባለስልጣናት ማከፋፈሉ ተጋለጠ፣

- ወያኔ ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ወጪ አድረጎ ካድሬዎቹን በድግስ አንበሸበሻቸዉ፣

- ቴዲ ይፈታ ብለዉ የጠየቁ ካድሬዎች በደህንነተ ታፍነዉ ተወሰዱ፣

- የወያኔ ባለስልጣናት በምግብ ተራ ባለመስማማታቸዉ ሽጉጥ ተማዘዙ፣

- በደቡብ ክልል በደራሼ ወረዳ በተከሰተ ግጭት ከ10 ሰዉ በላይ ሞተ፣ ቤት ንብረት ወደመ፣ የወረዳዉ ካቢኔ አባሎች ከግድያ ለጥቂት አመለጡ፣

የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል ።

ዝርዝሩን ከሚቀጥለዉ ገፅ ጀምረዉ ያንብቡ <<<<>>>>

ኢህአፓን ሽጦ ለወያኔ ያደረው የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ የብአዴን ሊቀመንበር እና የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር የነበረው ታምራት ላይኔ ከ12 ዓመታት እስራት በሁዋላ ከእስር መለቀቁ ታወቀ::

በገንዘብ ዝርፊያ ሰበብ በወያኔ መሀል በተፈጠረ የመጀመሪያ የፖለቲካ ሽኩቻ ለእስር የተዳረገው ታምራት ላይኔ በህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት ማስፈራራት እና ዛቻ እራሱን « ሌባ ነኝ ፤ዋልጌ ነኝ» እንዲል ተደርጎ ለእስር የበቃ መሆኑን ያስታወሱት ምንጮች ለ12 ዓመታት ለእስር ተዳርጎ የተለቀቀ መሆኑን ገለፁ::

የቀድሞው የኢህአፓ ታጋይ በሁዋላም የትግል ጉዋዶቹን በረሀ ላይ አሳልፎ የሰጠውና ከድቶ ለወያኔ ያደረው ታምራት ላይኔ በበረሀ እነ መለስ ዜናዊ ከከፈሉት መስዋዕትነት በላይ ከፍሎ የመጣ የነበረ ቢሆንም ገድሎ መጣል የሚያውቁበት እነዚሁ ቡድኖች ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ፤ ከብአዴን ሊቀመንበርነትና ከኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ ከገንዘብ ዝርፊ ጋር ሰበብ አድርገው ለእስር ዳርገውት ሲያሰቃዩት እና ሞራሉ እንዲላሽቅ አድርገው የፈቱት መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ በወያኔ መሀል በተፈጠረ ሽኩቻና ክፍተት ጣልቃ እንደይገባና እንዳይሳተፍ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጠው ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

በበረሀ በነበረው አውደ ውጊያ ከህወሀት ታጋዮች በላይ ከፍተኛ መስዋዕትነት እንደከፈለ የሚነገርለት ይኸው የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ በሽግግር መንግስቱ ወቅት የጠቅላይ ሚኒስትርነትና ከዛም በሁዋላ በተቁዋቁዋመው የፌዴራል መንግስት ተብዬ ውስጥ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ደረጃ የነበረው ቢሆንም በነመለስ ሴራ ተጠልፎ እራሱን በራሱ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አግልሎ ለእስር መዳረጉን ያወሱት ምንጮቹ 18 ዓመት እስራት ተፈርዶበት ሁለት ሶስተኛውን ጊዜ በማጠናቀቁ ከ12 ዓመት እስራት በሁዋላ ለመለቀቅ እንደበቃ ደግመው ገልፀዋል::

ከ12 ዓመት በፊት የወያኔን ፖለቲካ ሳይወድ በግድ የተነጠለው ይኸው ቀድሞ የወያኔ ባለስልጣን ታምራት ላይኔ ጊዜው ደርሶ የተፈታ ቢሆንም በወያኔ መሀል ከፍተኛ ችግር የተከሰተበት ወቅት ላይ በመሆኑ ቀድሞ በያዘው ዝና እና ታዋቂነት መሀላችን ገብቶ የበለጠ ችግር ሊፈጥርና ሊያባብስ ይችላል በሚል ስጋት የገባቸው እነመለስ ዜናዊ ከመፈታቱ 72 ሰዓታት በፊት በቲሌቪዥንና በሬዲዮ ከፍተኛ ቅስቀሳ ሲሰሩበት የቆዩ መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ለእስር ከመዳረጉ በፊት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወንበር እንዲለቅ በተደረገበት ወቅት « ይህንን ስርዓት ከሚቃወሙ ኃይሎች ጋር ወግኜ አልሳተፍም:: ይህንን ያደርጋል ብለው የሚጠብቁ ካሉ ተስፋ ቆርጠው እንዲያቆሙ » እያለ መግለጫ እንዲሰጥ የተደረገውን ዛሬ ከ12 ዓመት በሁዋላ እንደገና ደግመው ደጋግመው እያቀረቡት ከመሆኑም በላይ እነመለስ ውስጥ በተፈጠረ የፖለቲካ ሽኩቻ

ተሳታፊ ሆኖ ቂሙን ይውጣብናል በሚል ፍራቻ ብቻ አስቀድመው ቅስቀሳ እያደረጉበትና የማሸማቀቅ ስራ እየተሰራበት መሆኑን ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

የአማራን አልፎ ተርፎም የሀገሪቱን ህዝብ አስተዳድራለሁ ብሎ በጉልበት ስልጣን ላይ የነበረው ታምራት ላይኔ በአንድ ወቅት ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲል ብቻ ጅጅጋ ከተማ በመገኘት « የአማራውን ተወላጅ እረዱት፤ ግደሉት፤ ጨፍጭፉት፤... » በማለት መግለጫ በመስጠቱ በርካታ ሰዎች ለሞት የተዳረጉ ከመሆኑም በላይ በዚሁ ግለሰብ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ከህዝቡ እንዳስከተለበት ምንጮቹ አስታውሰዋል።

ከምዝበራ ጋር በተያያዘ በሚል ታምራት ላይኔ ለእስር ከመዳረጉ በፊት የህዝብ ተወካይነቱን በገዛ ፈቃዱ እንዲለቅ እቤቱ ድረስ ሄደው ከፍተኛ ስራ የሰሩት የህወሀቶቹ ባለስልጣኖች እና በሁዋላ ማነህ ባለተራ የወያኔ ባለስልጣን ተብሎ በካልቾ ተጠልዘው ከመንግስት እና ከፓርቲ ስልጣናቸው የተባረሩት ስዬ አብርሀ እና ጄ/ል ፃድቃን ወ/ ተንሳይ ከመለስ የተሰጣቸውን የቤት ስራ በመስራታቸው ሲወደሱና ሲሞካሹ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮቹ እነሱም ብዙ ሳይቆዩ በሰፈሩት ቁና ተሰፍረው ሊንቀረቀቡ እንደበቁም ጨምረው ገልፀዋል።

የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር እና የቀድሞው ኢህዴን በሁዋላ የብአዴን ሊቀመንበር የነበረው ታምራት ላይኔ ስልጣኑን እና የፓርቲ ከፍተኛ አመራርነቱን ተነጥቆ ለእስር በተዳረገ በጥቂት ዓመት ውስጥ በመለስ ትዕዛዝ ሲያስፈራሩትና ሲያስጨንቁት የነበሩት የህወሀት ባለስልጣናት ስዬ አብርሀ እና ጄ/ል ፃድቃን ወ/ ተንሳይ በህወሀት ውስጥ በተፈጠረ ክፍፍል ምክንያት በሰፈሩት ቁና ተሰፍረው ስዬ ለእስር ሲዳረግ ጄ/ል ፃድቃን ደግሞ ከስልጣን ለመባረር እንደበቃ የገለፁት ምንጮች ዛሬ ዙሪያውን በችግር ተወጥሮ ያለው መለስ ድንገት ከውስጥ ካለብኝ ችግር ጋር ተዳብሎ ቁጭቱን ይወጣብኝ ይሆናል በሚል ስጋት እንዳይፈታ ከፍተኛ ጥረት አድርጎ የነበረ ቢሆንም በወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት እምቢተኝነት ሊፈታ እንደበቃ አጋልጠዋል።

በተለይ አርባ አምስት ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣናት በመለስ ቢሮ በተሰበሰቡበት ዕለት የታምራት ከእስር መፈታት አለመፈታት ጉዳይ አንደኛው አጀንዳ እንደነበረ የገለፁት ምንጮች መለስ የተለያየ ምክንያቶችን እየደረደረ እንዳይፈታ ጥረት ቢያደርግም አዲሱ ለገሰን ጨምሮ ሌሎችም የህወሀትና የብአዴን ባለስልጣናት እንደማንኛውም እስረኛ ጊዜውን የጨረሰ በመሆኑ ከእስር ሊለቀቅ ይገባል በሚል አቋዋም በመያዛቸው መለስ ሳይወድ በግድ ሀሳቡን ሊቀበል እንደቻለ አጋልጠዋል።

በጥላቻና በተንኮል ውስጡ መርዝ የቆዋጠረው ግማሽ ኤርትራዊ እንደሆነ በተደጋጋሚ የሚነገርበት በረከት ስምኦን ከመለስ ጋር በመሆን ታምራት እንዳይፈታ የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን ቢደረድርም የህወሀትና የብአዴን ከፍተኛ ባለስልጣናት

በያዙት የፀና አቁዋም ሁለቱ ግለሰቦች ሳይሳካላቸው የቀረ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ታምራት ላይኔ የሚፈታበት እለት በዛን ስብሰባ ወቅት መወሰኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በስብሰባው ላይ የነበረው አንዱ አተካሮ ታምራት ከእስር ሲፈታ የሚይዘው ፖለቲካ አቁዋም ይወሰን ተብሎ የነበረ ቢሆንም በዚህም ጉዳይ ላይ ቀድሞ ከነበረበት አፈንግጦ ወደ ሌላ ፓርቲ ይሄዳል የሚል ግምት እንደሌላቸውና አሁንም ከዚህ አቁዋሙ የማያፈነግጥ መሆኑን የተስማሙበት ቢሆንም ሁሉም ባለስልጣናት እርስ በርስ እየተጠባበቁ ባለበት በዚህ ወቅት ታምራትን ለማጥመድ ያሰፈሰፉ መሆናቸውንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

የታምራት ልጆቹንና ባለቤቱን ጨምሮ ሲያሰቃዩ የነበሩት መለስ ዜናዊ እና ባለቤቱ አዜብ መስፍን በሚያደርሱባቸው ጫና ምክንያት በድብቅ ከሀገር ሊወጡ እንደበቁ እና ከውጭ ሆነው የተማፅኖ ደብዳቤ ቢልኩም ሰሚ አጥተው ቢቆዩም ከታሰረ 12 ዓመታት በሁዋላ ዓርብ ታህሳስ 9 ቀን 2001 ዓ. ም. ሊለቀቅ እንደበቃ አስረድተዋል::

ከእስር ሲፈታ የተቀበለችው ታናሽ እህቱ ስትሆን እሱም መግለጫ እንዲሰጥ ተደርጎ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብለትም ቀድሞ ሲሰድበው የነበረውን ህዝብ ሲያመሰግን እና ሲያወድስ ከመደመጡም በላይ ንግግሩ ሁሉ የክርስቲያን አማኝ ሆኖ እንደቀረበ ዝግጅቱን የተከታተሉ ተመልካቾች ገልፀዋል::

አይነጋ መስሎዋት እንዲሉ የህወሀቶቹ ቱባ ባለስልጣን የነበሩት እነ ስዬ አብርሀ በታምራት ላይኔ ላይ የሰሩት ሸፍጥ በነሱ ላይ አይደርስ መስሎዋቸው ቢሩዋሩዋጡም ብዙ ዓመታት ሳያስቆጥሩ ጣቶቻቸውን እያወዛወዙ ከደሙ ንፁህ ነን ቢሉም ሰሚ አጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ በ24 ሰዓት ውስጥ በተዘጋጀ ፀረ ሙስና ህግ ለ6 ዓመት ከነወንድሞቹ በእስር ሲማቅቅ እንደነበረ እና ሌሎቹም ከስልጣናቸው እንደተባረሩ የሚታወስ ነው::

ከህዝብ ላይ ዘርፈው በድርጅት ስም የተቁዋቁዋሙት የወያኔ የንግድ ድርጅቶች አመታዊ ትርፋቸውን ለባለስልጣናቱ ገንዘብ እንዲከፋፈሉ መደረጉ ተጋለጠ:: የወያኔ ድርጅት የሆነው ኤፈርት የተባለው ግዙፍ ካምፓኒ በስሩ ከ40 በላይ ትላልቅ ፋብሪካዎችና መሰል ተቁዋማትን አካትቶ የያዘ ሲሆን ይህንን ድርጅት የሚመራውና የሚቆጣጠረው ህወሀት መሆኑን የገለፀው ዘገባ ሰሞኑን በድብቅና በሚስጥር ለህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት ዓመታዊ ትርፍ በሚል ከፍተኛ ገንዘብ እንደተሰጣቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ::

በ1983 ዓ. ም. ወያኔ ስልጣን ላይ እንደወጣ ከህዝብ በዘረፈው ገንዘብ የተቋቋቋቋመው ይኸው ግዙፍ ድርጅት ንብረትነቱ የህወሀት ነው ተብሎ እየተነገረ የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ስሙ ካልሆነ በስተቀር በጣት የሚቆጠሩ ባለስልጣናት ብቻ ንብረት መሆኑን የሰሞኑ ዓመታዊ ትርፍ ገንዘብ ክፍፍል አመላካች መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

የቀድሞው መከላከያ ሚኒስትር የነበረውና ከህወሀት ክፍፍል በሁዋላ ለእስር ተዳርጎ የነበረው ስዬ አብርሀ የበላይ ተቆጣጣሪነት ሲመራ የነበረው ኤፈርት የተባለው የህወሀት ድርጅት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህወሀት ስም የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ስሙ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የግለሰቦች መሆኑን ያረጋገጠ ነው ሲሉ ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ሰማዕት በሆኑ የህወሀት ታጋዮች ስም አቋቋቁመውት የነበረውን ድርጅት ከመለስ ጀምሮ 20 የህወሀት ባለስልጣናት በምስጢር እየመዘበሩት እና እየተጠቀሙበት መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው አጋልጠዋል፡፡

በህዝብ ደም እና እንባ መነገድ የሚችሉበት እነ መለስ ዜናዊ ለብዙ ዓመታት አብረዋቸው ሲታገሉና መስዋዕት በሆኑ ጉዋዶቻቸው ስም ድርጅቱን አዋቅረው የነበረ ቢሆንም ነባር ታጋዮችን ከስራ በማባረርና በማፈናቀል እንዲሁም የጎዳና ተዳዳሪ ካደረጉ በሁዋላ አሁን የድርጅቶቹ ባለቤቶች እነ መለስ ብቻ ሆነው አመታዊ ትርፍ መጠኑ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ብር መከፋፈላቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በሁሉም የንግድ ዘርፎች በሀገሪቱ ያለግብር እና ያለ ቀረጥ ክፍያ በነፃ ተሰማርቶ የሚገኘው የወያኔ ግዙፍ ድርጅት በሞቱት ሰማዕታት እና አካላቸውን ባጎደሉ ታጋዮች ስም ከህዝቡ ላይ ገንዘብ እየመዘበሩ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮቹ ዛሬ ሁሉም በተዳከመበት ወቅት የህወሀት ከፍተኛ አመራሮች ብቻ ባለ አክሲዮኖች ሆነው በምስጢር እየነገዱ መሆናቸውንና ሰሞኑንም አመታዊ ትርፍ መከፋፈላቸውን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው እንዲሉ እነመለስ የራሳቸው ደጋፊ ለሆኑት ብአዴኖች ለስሙ አምባሰል እና ጉና በሚል አናሳ ድርጅት አቋቁመውላቸው እየተንቀሳቀሱ ቢሆንም የአንበሳውን ድርሻ የወሰዱት ህወሀቶች ሰሞኑን ከፍተኛ ገንዘብ እያግበሰበሱ መሆናቸውን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በጮሌነት ከተራ ተዋጊነት እስከ ሀገር መሪነት የደረሱት እነ መለስ በረሀ እያሉ የገዛ ጉዋዶቻቸውን በጥይት እየገደሉ የመጡ መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ ስልጣን ላይ ከወጡ በሁዋላም በግምገማ ሰበብ ገሚሱን ለእስር ሌላውን በመግደልና በማባረር ስልጣናቸውን አደላድለው ግዙፍ ድርጅቱን በሚስጢር መውረሳቸው እጅግ አሳፋሪና

አሰዛዛኝ ነው ሲሉ ድርጊቱን የሰሙ የቀድሞ ታጋዮች እንባ እየተናነቃቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል።

ሀገሪቱ በኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ እየዳከረች ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ እራሱ በህዝቡ መሀል የፈጠረውን ግጭት መልሶ ለመጠገን በሚል ሰንካላ ምክንያት እጅግ ከፍተኛ ብር ወጪ ማድረጉ ተጋለጠ።

ተፋቅረው የኖሩት የሀገሪቱ ህዝቦች መሀል ጣልቃ እየገባ ለማጋጨትና ለማጫረስ ሙከራ ቢያደርግም አልሳካ ሲለው የተፋውን ምራቅ መልሶ እየዋጠ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በሚል ለይስሙላ ለማክበር ሲሩዋርዋጥ መሰንበቱ አስገራሚ መሆኑን ጉዳዩን የተከታተሉ ወገኖች ገለፁ።

የብሔር ብሔረሰብ ቀን በሚል ከህዳር 26 ቀን እስከ ታህሳስ 2 ቀን ድረስ በተለያዩ አዳራሾች የወያኔ ካድሬዎችን እየሰበሰቡ ድል ያለ ድግስ በመደገስና በመጋበዝ በህዝብና በሀገር ሀብት እየቀለዱበትና እየተጫወቱበት የከረሙ መሆኑን የገለፁት እነዚሁ ወገኖች በተለይ ለእያንዳንዱ ካድሬ የውሎ አበል በሚል ከፍተኛ ገንዘብ እንደተሰጣቸው ገልፀዋል።

ከየወረዳውና ከየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ የወያኔ የቀበሌ ተመራጮችንና ካድሬዎችን እንዲሁም ቤተሰቦቻቸውን መርጠው አዲስ አበባ ላመጡዋቸው ከ10 ሺህ በላይ ለሆኑት ገጠሬዎችና ባለስልጣኖቻቸው ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ ህዝብ በኑሮ ውድነትና በርሀብ እየተሰቃየ ባለበት በዚህ ወቅት ህዝቡን መደጎም ይመስል ላይሆንላቸው በህዝቡ መሀል ችግር እንዲፈጠር እራሳቸው ሲቆፍሩትና ሲምሱት ለነበረው ጉዳይ ይህንን ሁሉ ገንዘብ ማውጣታቸው እጅግ አሳዛኝ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በንዴት ሲገልፁ መደመጣቸውን ዘገባው አስረድቶዋል።

ህዝቦች ተፋቅረው፣ ተዋደወደውና ተግባብተው እንደቀድሞው ከኖሩ ለስልጣኔ ያሰጋኛል በሚል ወያኔ አንዱን ብሔር ከሌላው ብሔር ፣አንዱን ቀበሌ ገበሬ ማህበር ከሌላው ላይ እየነጠቀ ለሌላው እየሰጠ ፣የአንዱን የግጦሽ ቦታ ለሌላው እየቸረ ክፍፍል እንዲፈጠር እያደረገና እያጣላ በሀገሪቱ ታሪክ ታይተው እና ተሰምተው የማያውቁ ግጭቶች እንዲከሰቱና ብዙ ህዝብ እንዲያልቅ፣ ቄአቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ሲያደርግ ሰንብቶ ዛሬ የብሔር በሔረሰብ ቀን በማለት ከሀገሪቱ አቅም በላይ ወጪ መድቦ የራሱን ካድሬዎች በድግስ ሲያንበሻብሽ መሰንበቱ ታውቆዋል።

ለእያንዳንዱ የወያኔ ካድሬ በቀን 200 ብር በላይ እየተከፈለው የምግብና ሌሎች ወጪዎች ከህዝብ ካዝና ተሰጥቶዋቸው ሲምነሸነሹ የሰነበቱት እነዚሁ ወያኔዎች

በምግብ  አቀባበል ተራ መጠበቅ ላይ ሳይቀር ሲስገበገቡ እና እርስ በርስ ሲሰዳደቡ እንደነበረም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

በቦሌ ሚሊኒየም አዳራሽ  ውስጥ ህዳር 28 ቀን 2001 ዓ. ም.በተዘጋጀው የእራትና የሙዚቃ ድግስ ላይ ከቀበሌ ካድሬዎች እስከ መለስ ዜናዊ ድረስ የተገኙ ሲሆን በተለይ ዝቅተኛ ካድሬዎች ምግብ ለመቀበል ያደረጉት እሽቅድድም እስከ ሽጉጥ መማዘዝ ድረስ ደረሰው እንደነበረ የደረሰን ዘገባ ገልፆ ጥቂት ያልሆኑትም በነበረው መስተንግዶ ተበሳጭተው አዳራሹን ጥለው ወደ ማደሪያቸው እንደተመለሱ ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

ለሆዳቸው እንጂ ለህሊናቸው የማይኖሩት እነዚሁ የወያኔ  ሹማምንት በነፃ የህዝብን ሀብት ለማግበስበስ እንደ አሞራ ሲሻኮቱ እንዳመሹና እንደተጣሉ የገለፀው ዘገባው በቀረበው የሙዚቃ ዝግጅት ደስተኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው «ቲዲ! ቲዲ! ቲዲ! » እያሉ በከፍተኛ ድምፅ ሲጮሁ መደመጣቸው በአዳራሹ  የነበሩት እነመለስ ዜናዊ በንዴት መልካቸው ሲቀያየር ያስተዋሉ በቅርበት የተከታተሉ ወገኖች  ገልፀዋል፡፡

በተለይም የአዲስ አበባ አፍለኛ እና ከአማራ ክልል የመጡ  የወያኔ ካድሬዎች በአዳራሹ ውስጥ «ቲዲ ይፈታ» እያሉ በከፍተኛ ድምጽ ሲጮሁ መደመጣቸው ያበገናቸው እነመለስ በቪዲዮ ምስላቸው ተቀርፆ ለደህንነት እንዲተላለፍ መደረጉንም ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩት ወገኖች አስረድተዋል፡፡

ቲዲ አፍሮ ይፈታ የሚለው  የካድሬዎቹ ጥያቄ   ያልተጠበቀና ሊሆን ይችላል ተብሎ ሳይታሰብ በመከሰቱ የወያኔው መሪ መለስን ጨምሮ በርካታ ባለስልጣናት ከመበሳጨታቸው የተነሳ አስር ጊዜ ከመቀመጫቸው ቁጭ ብድግ  እያሉ ሲመለከቱ እንደነበረ የገለፁት እነዚሁ በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖች ይህን ጥያቄ  ሲያቀርቡ የነበሩትን በሙሉ በስውር ካሜራ እንዲቀረፁና ለደህንነት ባለስልጣናት ፊልሙ እንዲሰጣቸው መደረጉን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የደህንነት ባለስልጣኖቹም በስውር ካሜራ ተቀርፆ እጃቸው በገባው  ፊልም በመመርኮዝ በዕለቱ ቲዲ ይፈታ የሚለውን  ጥያቄ ያቀረቡ ናቸው የተባሉ የወያኔ ካድሬዎችን ከአዳራሽ ውስጥ  እየመረጡ ለስራ ትፈለጋላችሁ እያሉ ወደአልታወቀ ቦታ የወሰዱዋቸው መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

በህዝብና በሀገር ሀብት እየቀለደ ያለው የወያኔ ቡድን ለአንድ ሳምንት ዝግጅት በሚል ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ያደረገ ሲሆን በአንፃሩ ግን ህዝቡ በኑሮ ውድነት ችግር ውስጥ ተዘፍቆ መውጫ ቀዳዳ አጥቶ የስንግ ተይዞ መኖሩን እያወቁ በህዝቡ ቁስል ላይ እንጨት እየሰደዱበት  ይባስ ብለው ችግሩን እያባባሱበት መገኘታቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ነው  ሲሉም  አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ወያኔ የብሔር ብሔረሰብ ቀን አከብራለሁ እያለ እያቅራራ ባለበት በዚህ ወቅት በደቡብ ክልል ለዘመናት ተከባብሮና ተፋቅሮ የኖረውን ህዝብ እርስ በርስ አጋጭተው አንድ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሙሉ በሙሉ በእሳት እንዲወድም ማድረጋቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ከታህሳስ 4 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ ለሶስት ተከታታይ ቀናት በተደረገ ግጭት ከ10 ሰዎች በላይ የተገደሉ ሲሆን ከ20 በላይ ሰዎች ደግሞ ክፉኛ ቆስለው በቃሬዛ እተጉዋጉዋዙ በአቅራቢው ወደሚገኘው የህክምና ጣቢያ የተወሰዱ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

በደራሼ ወረዳ ሁለት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪዎች መሀከል ከዚህ ቀደም በግጦሽ መሬት ሳቢያ ግጭት ይፈጥሩ የነበረ ቢሆንም በሀገር ሽማግሌዎች እርቅ ይወርድና ሰላማዊ በሆነ መልኩ ይጠናቀቅ እንደነበር የገለፀው የደረሰን ዘገባ ወያኔ በሀገር ውስጥ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ምክንያት ህዝቡ መሀል እርስ በርስ ግጭት እንዲፈጠር አድርጎ መልሶ ሽማግሌ በመሆን ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲል የፈፀመው ወንጀል መሆኑን የገለፀው ከአካባቢው የደረሰን ዘገባ ለአንደኛው ወገን የጦር መሳሪያ አስታጥቆ እየሰጠ አንደኛውን ደግሞ እየነጠቀ ጀሌ እያደረገ ከፍተኛ እልቂት እንዲፈጠር ማድረጉን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

ችግሩ ከተከሰተ ሶስት ቀናት በሁዋላ የወረዳው አስተዳዳሪን ጨምሮ ሌሎች ባለስልጣናት ግጭቱ ወደተከሰተበት አካባቢ የተጉዋጉዋዙ ቢሆንም « ይህንን እልቂት ያመጣችሁት እናንተ ናችሁ » በሚል ህዝቡ ዙሪያቸውን ከብቦ ለመግደል ሙከራ አድርጎ የነበረ ቢሆንም ባለስልጣናቱ እግሬ አውጭኝ በማለት አምልጠው መሸሻቸውን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በህዝብ ላይ ሆን ተብሎ ሽርና ተንኮል እንዲሸረብ አድርገው የብዙ ሰው ህይወት ከጠፋና ቤት ንብረት ከወደመ ከሶስት ቀናት በሁዋላ የፌዴራል ፖሊስ ወደ አካባቢው የገባ ቢሆንም ችግሩ ጋብ ያለ ይሁን እንጂ ጨርሶ ያልተቀረፈ መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል::